## የኢትዮጵያዊን ሙስሊሞች ዓለም አቀፍ ምክር ቤት (ግሎባል ካውንስል ኦፍ ኢትዮጵያን ሙስሊምስ) በቶሮንቶ ያዘጋጀው ሕዝዝባዊ ስብሰባ በተሳካ ሁኔታ ተካሄደ። የኢፖእአኮ ፕሬዚዴንት አቶ ዓሊ ሁሴን የስብሰባው የክብር እንግዳ ነበሩ

ከስብሰባው ተሳታፊዎች

ግሎባል ካውንስል ኦፍ ኢትዮጵያን ሙስሊምስ በመባል የሚታወቀው አለም አቀፉ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ምክር ቤት በኦክቶበር 12, 2014 አ.ም በቶሮንቶ ካናዳ ያዘጋጀው ህዝባዊ ስብሰባ ኢትዮጵያውያን ታዳሚዎች በተገኙበት በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል።

ይህ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ለመነጋገር የተጠራው ስብሰባ ብዛት ያላቸው ኢትዮጵያውያን የተካፈሉበት ሲሆን የእለቱ የክብር እንግዳ ታዋቂው የሰብአዊ መብት ተሟጋችና የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ **SOCEPP** ፕሬዚደንት አቶ አሊ ሁሴን ነበሩ። ከተወሰነለት ጊዜ ዘግየት ብሎ የተጀመረውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት የመሩት አቶ ኢብራሂም አቶ አሊን ወደ መድረኩ የጋበዙት አቶ አሊ ሁሴን በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብቶች ረጅም ተጋድሎ ታሪክ ውስጥ ያካሄዱትን እልህ አስጨራሽ ነገር ግን በድል የታጀበ አስተዋፅኦ በማወደስ ሲሆን ለአብነት ያህልም አቶ አሊ ሁሴን ለረጅም አመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሰብአዊ መብቶች መከበር ላበረከቱት ተጋድሎ በ2009 እና በ 2013 የ Human Right Commitment Award ተሸላሚ መሆናቸውንና በቅርቡም በዊኒፔግ ካናዳ በአለም በአይነቱ የመጀመሪያ በሆነው የካናዳ የሰብአዊ መብቶች ሙዚየም (**Canadian Museum for Human Rights** (**CMHR**) ውስጥ በኢትዮጵያ አንድ ትውልድን የፈጀው የቀይ ሽብር ታሪክ ከሌሎች እንደ ናዚ ሆሎኮስትን ከመሳሰሉ የአምባ ገነኖች የፍጅት ታሪክ ጎን እንዲቀመጥ ማድረጋቸውን ገልፀዋል። ከአቶ አሊ በስተቀር በዚህ አለም አቀፍ የሰብአዊ መቶች ሙዚየም ውስጥ ሥፍራ የተሰጣቸው ሌላው አፍሪካዊ የደቡብ አፍሪካው ኔልሰን ማንዴላ ብቻ ናቸው።

አቶ አሊ ሁሴን ንግግራቸውን የጀመሩት የሰብአዊ መብትን ምንነት በማስረዳት ሲሆን በእድሜያቸው ሦስት አምባገነን ሥርአቶችን እዳዩና መጠናቸው ይለያይ እንጂ ሁሉም ሥርአቶቻቸውን ዘለዓለማዊ ለማድረግ ሀይማኖቶችን በመከፋፈል አንዱ ከሌላው ለይቶ በማየት እንዴት ላገዛዛቸው ይጠቀሙበት እንደነበረ በስፋት አስረድተዋል። ታሪካዊው የ1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮት ይዞ ከተነሳባቸው ጥያቄዎች የሃይማኖቶች እኩልነትና ነፃነት አንዱ እንደነበረና ይህም ጥያቄ ዛሬም ድረስ ምላሽ ካለማግኘቱም በላይ ጭቆናና አፈናው በከፋ ሁኔታ መቀጠሉን አስረድተዋል። ላለፉት ሦስት አመታት ያህል በፅናት የቀጠለውም የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ትግል ወያኔ ትግሉን ከህዝቡ ለመነጠል እንደሚዋሸው ለሥልጣን ሳይሆን ለእምነቱ መብት መከበር እንደሆነም በሚገባ አብራርተዋል።

በመቀጠልም ያትውልድ ከዛሬ 42 ዓመት ጀምሮ ለሃይማኖት እኩልነት ለሙብትና ለዲሞክራሲ እንደሞተ ወደፊትም ትግሉ ብዙ መስዋትነት እንደሚጠይቅ አስረግጠው አስረድተዋል።

ከዚህም በማያያዝ አቶ አሊ ሁሴን ሲያብራሩ ድርጅታቸው **SOCEPP** በተለያዩ የአፍሪካ እስር ቤቶች ውስጥ ታግተው ስለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ሁኔታ ለማወቅ መረጃ መሰብሰብ ማስፈለጉን

ስላመነበትና ይህንኑም ተልዕኮ እሳቸው እንዲያከናውኑ ስለወከላቸው እሳቸውም ተልዕኮውን ተቀብለው በኬንያ፣ በዩጋንዳ፣ በቡሩንዲና በደቡብ አፍሪካ እስር ቤቶች ውስጥ በመገኘት በየእስር ቤቶቹ ውስጥ የተመለከቱትን በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለውን ሰቆቃ በተለይም በሴት እህቶቻችን ላይ የሚፈፀመውን ግፍ ሲያስረዱ አድማጩ እንባውን መቆጣጠር እስኪያቅተው ስሜቱ ተነክቷል።

በንግግራቸውም መጨረሻ ከቤቱ ለተነሱት ጥያቄዎች አጥጋቢ ምላሽ የሰጡ ሲሆን በየዝግጅቱም ጣልቃ አቶ አሊ ሁሴን ከቤቱ በቀረበላቸው ጥያቄ መሰረት ተወዳጅና ቀስቃሽ የሆኑትን የግጥም ሥራዎቻቸውን ከአንድም አራት ግዜ ለተሰብሳቢው ያቀረቡ ሲሆን ታዳሚውም ስሜቱን በእንባ በታጀበ ጭብጨባ ገልፆላቸዋል።

በመጨረሻም ትግሉ የጋራ መሆኑን በማስረገጥ ለጋራ ሀገራችንና ነፃነታችን በጋራ መታገል እንደሚገባ አሳስበው ስብሰባው በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል።